## <u>*ያ ታማኝ በየነ!*</u>

<u>*ከጥበበ ሣሙኤል ፈረንጅ፡*</u>

ከጎንደር ከተማ የተነሣው መብረቅ፡
አዲስ አበባ ውስጥ ጥርስ ፀሐይ ሲያስሞቅ፤
ያ ታማኝ በየነ ወጣ አሉ ከአፍሪካ፡
ትግል ሊያነሣሣ ሰሜን አሜሪካ።
ወቴን ሲቀሰቅስ በየጦሩ ግንባር፡
ፊት ለፊት ሲጋፈጥ ደጀን ሆኖ ለአገር፤
አዝናንቶ አስቆ ዜጋውን ሲያስተምር፡
ወኔ ሲያነሣሣ ጀግና ሲያጠነክር፤
መች ከደርግ ነበር እሱ የወገነው፡
ለሃገር ክብር እንጂ በፅናት የቆመው።

ገባሁ፡ ገባሁ ብሎ ኢሕአዴግ ሲያጉዋራ፡
ከፊሉ ሲጨነቅ ከፊሉ ሲፈራ፤
ለሲኤንኤን ዜና ለአለም ወሬ አውታር፡
ደፍሮ የሚናገር ያው ታማኝ ነበር።
ኢሕአዴግ ገስግሶ አገር ሲቆጣጠር፡
ኤርትራን ሊነጥል ቀናትን ሲቆጥር፤
በማንአለብኝነት ሻዕብያ ሲወጣጠር፡
ታማኝ ውጋት ሆኖ የጫማ ውስጥ ጠጠር፤
መስቀል አደባባይ ስቴድየም አልቀረው፡
ባገኘው መድረክ ላይ ኢትዮጵያ ብሎ ነው፤
በነጋ በጠባ ለሕዝቡ የጮኸው።
ታድያ ምን ያደርጋል መቼም አልታደለ፡
ባንዲራውን ለብሶ ኢትዮጵያ ስላለ፤
እንደ ወንጀለኛ ልክ እንደበደለ፡
ወታደር ቀጥቅጦ ወሰደው ዘብጥያ፤
አንድ ነች አገሬ አንድ ነች ኢትዮጵያ፡
አትገነጣጠል ይከበር ወሰንዋ፤
ባሕር አልባ አትሁን ቀይ ባሕር ነው በርዋ፡
ብሎ ስለጮኸ እውነት ስላወራ፤
ጨለማ ቤት ገባ ታሸ በመከራ።
እውነቱ ሊወጣ ገበናው ሊገለጥ፡
ወያኔና ሻዕብያ እንደዚህ ሊፋጠጥ፤
ጠበኞች ሊሆኑ ላይቀር ግጭታቸው፡
ውሻን ውሻ በላው ሊሆን ነገራቸው፤
እንደታማኝ ያለ ከአገር ተሰደደ፡
ለእውነት በመቆሙ ስንቱ ተማገደ።

በፖለቲካ እምነቱ ስትፈልጉ ጥሉት፡
አርቲስት ነው ታማኝ በሙያው አክብሩት፤

ቁም ነገርና ቀልድ እየቀላቀለ፡
አንዴ በዳንኪራው ቀጥሎም በእስክስታ ሕዝብ እያባበለ።
እንደ አስቴር አወቀ ወየው ጉዴ ሲል፡
እንደ ማይክል ጃክሰን እግሮቹን ሲነቅል፣
እንደ ጎንደሬዎች እስክስታ ሲመታ፡
ዳንኪራ ሲረግጥ ልክ እንደ ወላይታ፣
የጥሌን ዘፈኖች በቅጥ ሲያዜማቸው፡
በጭፈራ አጅቦ እንደየወጋቸው፣
ግጥሙን ሲያነበንብ በከያኒ ክህሎት፡
ስሜት በሚነካ የመረዋ አንደበት፣
በለዛ ጠቅልሎ ቁምነገርና ቀልድ፡
ከመድረክ ላይ ሆኖ ሰዉን ሲያስተናግድ፣
ሴቱን ሲያባብል በዓይኑ እየጠቀሰ፡
ወንዶቹን ሰላም ሲል እያጎነበሰ፣
ማን ጎበዝ ሰው አለ እንደታማኝ ብርቱ፣
በሙያው ተከብሮ ይባል እንጂ አንቱ።

በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ፣ በሕይወት እያሉ፣ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ውዳሴና ምስጋና ያገኙ ኢትዮጵያውያን እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ብዙዎች ቁርጥ የኢትዮጵያ ልጆች፣ ለሃገርና ለሕዝብ ያበረከቱትን አስተዋፅኦ እንዳወቅንላቸው እንኳዋ ሳናሳውቃቸው አልፈዋል። ይህን ባሕል ልንቀይርና ባለውለታዎቻችንን ውለታቸውን ልናሳወቅ ይገባናል። ያን ስናደርግ ሌሎች ጀግኖች ፈለግ ተከታዮች በመሆን ለፍትሕና ለሰብዓዊ መብት ለሚደረገው ትግል ጉልሕ አጋዥ፣ ጉልህ ተዋናይ ይሆናሉ። አርቲስት ታማኝ በየነ፣ ኢሕአዴግ የስልጣን ኮርቻው ላይ ገና መፈናጠጥ ሳይጀምር ነው፣ ስለአዲስ መጭው ገዥ ስጋቱን የገለጠው፣ የታማኝ በየነ ትግል ግን በዚህ ብቻ አላቆመም። እንደዛሬው፣ የተቃዋሚ ድርጅት እንደ አሸን ባለሞላበት ጊዜና ለሕዝብ መብት የአደባባይ ተሟጋች ባልነበረበት ወቅት፣ በአብዮት አደባባይ፣ በአዲስ አበባ ስታድዮምና በሌሎች ሕዝባዊ መድረኮች፣ ታማኝ በየነ ደረቱን ለጥይት ሰጥቶ ለሕዝብ ተሟግትዋል። ለዚህም ድፍረቱና ድምጽ አልባ ለነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልሳን በመሆን ለሕዝብ በመጮሁ፣ እምባውን በአደባበይ በማንባት ብሶቱን ለመግለፅ ለሰጋው ኢትዮጵያዊ፣ እንባውን በማንባት ብቻ ሳይሆን አንገቱን ቀና እንዲያደርግ የሕዝብ እምባ በማበሱ፣ ታማኝ፣ በኢሕአዴግ ገዥዎች አይቀጡ ቅጣት ተቀጥትዋል። አርቲስት ታማኝ በየነ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታና የኢትዮጵያ ውድ ልጅ ነው። ምንም እንኳዋ ለአርቲስት ታማኝ እንደሆሊዉድ ቱጃሮች በቀይ ምንጣፍ የሚገባውን ክብር ልንሰጠው ባንችልም፣ ባለን አቅም ስለውለታው፣ ስላበረከተው አስተዋፅኦና ለሌሎች ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች መልካም አርኣያ በመሆኑ እውቅና ልንሰጠው ይገባል። ያን እድል አስክናገኝ ግን ለአርቲስት ታማኝ በየነ ያለኝን ታላቅ አክብሮት በዚህች ግጥም እንድገልጽ ይፈቀድልኝ።